ተ የጸሎት አደራረግና የመናፍስት ውጊያ አካሄድ ተ

1ኛ✔ መጀመሪያ ጸሎት ቤታችሁ(ትንሽዬ ቤተመቅደሳችሁ) ከመግባታችሁ በፊት ፊታችሁንና እጅ እግራችሁን ታጥባችሁና ንጹሕ ሆናችሁ ተዘጋጁ።
2ኛ✔ ነጭ አልባስ ብትለብሱ መልካም። አሊያም ለቤተክርስቲያን ያዘጋጃችሁትን አልባስ። ቢጠፋ ቢጠፋ ግን ነጠላ አይጠፋም።
3ኛ✔ እንደ ገባን በመቆሞ ልክ ከሥላሴ ስዕል ትይዩ እንሆንና ሦስት ጊዜ እናማትባለን። ካማተብንም በኋላ በቅዱሳን ስሞች ጸሎታችንና ስግደታችንን እንባርካለን።
4ኛ✔ በመቀጠል መዝሙር 22'ን መጸለይ
5ኛ✔ አስከትለን በዛው "አባታችን ሆይ" እንላለን
6ኛ✔ ቀጥለን ከቆምንበት የሥላሴ ትይዩ ስዕል ሆነን የአምልኮት ስግደት መስገድ።
7ኛ✔ ቀጥለን፤ መናፍስትን ግንባር ላይ አስረን፤ ከጸሎት ስዕለ አድኖ ጠጋ ብለን ተንበርክከን የሰዓቱን ጸሎት ማለትም ለምሳሌ ምሽት 3:00 ከሆነ ጸሎተ አርጋኖን፤ ቀን 11:00 ከሆነ ውዳሴ ማርያም ማድረስ።
8ኛ✔ በአባታችን ሆይ የሰዓቱን ጸሎት መዝጋት
9ኛ✔ የግል ጸሎታችንን ማድረስ (ርዕስ ሰጥተን የምናደርሰው ወይንም የምንጠይቀው የግል ጸሎት)
10ኛ✔ ጸሎቱን ካደረስንም በኋላ መቁጠሪያችንን በመጠቀም መለኮተ ስሞችንና የቅዱሳንን ስሞች እየጠሩ የመሸጉ ክፉ መናፍስትን ለማድከም ጀርባን፣ ሁለቱንም ትከሻዎች፣ ጭንቅላትንና ሆድን በእምነት መቀጥቀጥ። (አሊያ ሁላችሁም ጀርባ ላይ ታሰሩ ብለን መቅጥቀጥ)
11ኛ✔ በመቀጠል ጠላት ከጀርባ ወደ ግንባር ሄዶ እንዲታሰር በመለኮተ ስሞቹና በሌሎቹም ቅዱሳን እናዘዋለን
12ኛ✔ በመቀጠል የአምልኮት ስግደት መስገድ። ግንባር ላይ ስላሰርነው፤ ግንባራችንን የእንጨት መስቀል ላይ አሊያ ቅዱሳን ስዕላት ላይ ወይንም ጸሎተ መጽሐፍ ላይ እያስነካን ስንሰግድ በጣም ይቃጠላል
13ኛ✔ ጸሎታችንንና ስግደታችንንም ተቀበለን ብለን እንጸልይና በአባታችን ሆይ እንዘጋለን።

Scanned with CamScanner